# የኢ/ኦ/ተ/ቤ የኢንሳይክሎፔዲያ (የመዝገበ አእምሮ) ዝግጅት የውስጥና የውጭ አርትዖት መምሪያ

(EOTC Encyclopaedia Internal and External Editorial Guidelines)

## በማኅበረ ቅዱሳን የመዝገበ አእምሮ ዝግጅት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዝገበ አእምሮ ዝግጅት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሃያ (20) ዓመታት አሥራ ሁለት (12) ጥራዞችን ለማሳተም ያቀደ ሲሆን፣ በዋናነትም በጥራዞቹ ላይ ማሳተም ለሚፈልጉ ተመራማሪዎችና የተለዩ የጥናት ወረቀቶች የሚታረቱበትን፣ የሚመረጡበትንና የማይመረጡበትን መንገድ የሚጠቁም በአጠቃላይ ለአርታዕያኑና ለጸሓፍያኑ መምሪያ በመሆን የሚያገለግል ሰነድ ነው፡፡ መዋቅሩ በሁለት ዐበይት ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን እነሱም፣

### ፩.የውስጥ አርትዖት መመሪያ (Internal Editorial Guideline)

### ፩.፩. የመገምገሚያ (የአርዖት) መመሪያ (Editorial Guideline)

- ጥናቱ ዋና ርእስ እንዳለው ማረጋገጥ፣
- ንኡሳን ርእሶች አይኖሩትም፣
- የጸሓፊው ሙሉ ስም የትምህርት ደረጃ፣ አድራሻና የሚሠራበት መሥሪያ ቤት መጻፉን ማረጋገጥ
- ጥናቱ በሦስተኛ መደብ ድምጽ የተጻፈ መሆን አለበት
- በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎች ከስር በተገለጸ መንገድ የጥቅስ አወሳሰድና የመረጃ ምንጭ አጠቃቀስ የተከተሉ መሆኑን ማረጋገጥ
- አጥኚዎች ተገቢውን የአማርኛ ፊደል አጠቃቀም መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤ የግዕዝ ቃላትን በጥናቱ ውስጥ ስናገኝ ተገቢውን የግእዝ ፊደል መጠቀማቸውን መፈተሽ
- የጥናቱ ይዘት ኦርቶዶክሳዊ ዶግማና ትውፊት የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ
- ሳይንሳዊ የጥናትና ምርምር አካሄድ መከተሉን ማረጋገጥ
- ጥናቱ በተገለጸው የገጽ ገደብ የተቀነበበ መሆኑን ማረጋገጥ
- ጥናቱን የበለጠ በማጉላት አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል ተብለው የሚመረጡ ካርታዎች፣ ፎቶዎች፣ ሥእሎች ወዘተ. ተገቢው መግለጫ(caption) የተሠራላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

- ቁጥሮች ወይም ሌሎች መረጃዎች ሲቀርቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ

## ፩.፪. የሥነ-ምግባር (የሰብእና) መመሪያ (Ethical Behavioural Guideline)

- የአርትዖት ቡድኑ ለተራማሪዎች ተገቢውን ክብር መስጠት መቻል አለበት።
- የአርትዖት ኮሚቴው የቀረቡለትን የጥናት ወረቀቶች ተገቢውን ማስተካከያ ወይንም አስተያየት ከመስጠት ውጭ የጥናት ውጤቶቹ ለሌሎች አካላት ተላልፈው እንዳይሰጡ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት።
- በጥናቱ ላይ የተለዩ ድክመቶችም ይሁኑ ጥንካሬዎች ከተገኙ ተለምዷዊ ከሆኑ የአስተያየት አሰጣጥ ውጭ በተጋነነ መልኩ ለጥናት አቅራቢዎች አላስፈላጊ አስተያየት መስጠት የለበትም (ምሳሌ ኀይለቃል የተሞሉና ሰብእና የሚነኩ አስተያየቶች እና የተጋነኑ ሙገሳዎች)
- ተገቢውን አስተያየት ከሰጠ ወይንም ከሰጠች በኋላ ለተመራማሪው በሦስት ቀናት ውስጥ እንዲመልስ ይገደዳል።
- ተመራማሪዎች ለተጨማሪ ውይይት ወደቢሮ የሚመጡ ከሆነ ተገቢውን የማስተናገጃ ሰዓት በመመደብ የማማከር አገልግሎት መስጠት መቻል አለበት።

## ፩.፫. የመሰረዝ ወይንም የማስቀረት መመሪያ (Rejection or Deletion Guideline)

- **የአርትዖት ቡድኑ የቀረቡለትን የጥናት ውጤቶች ያለቅድመ ሁኔታዎች እንዲሰርዙ የሚያስችሉት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው**

1. የቀረበው የጥናት ወረቀት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ዶግማ፣ሥርአተ እምነትና ትውፊትን ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ
2. የቀረበው የጥናት ወረቀት ቤተ ክርስቲያናዊ ይዘት ሳይኖረው ሲቀር

3. መረጃዎቹ ከተለያዩ ቦታ ተወስደው ነገር ግን በተገቢው መንገድ የመረጃ ምንጭ ሳይቀመጥላቸው ሲቀር (Plagiarism)

- **የአርትዖት ቡድኑ ለመሰረዝ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጥባቸው ግድፈቶች**

    1. አጥኚው/ዋ በአርትዖት ቡድኑ አማካኝነት የተሰጡትን አስተያየቶች በአግባቡ ማስተካከል የማይችል ከሆነ፤
    2. በውስጥ መመሪያው ላይ በዝርዝር የቀረቡትን ቅርጽ(format) ያልተከተለ ከሆነ

ነገር ግን ሁለት የአርትዖት ኮሚቴ አባላት ወይንም ጥናቱ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጥናቱን ተመልክተው ከላይ በተዘረዘሩትና ተዛማጅ ምክንያቶች እንዲወድቅ ካመለከቱ፡ የመዝገበ አእምሮ ዝግጅት አስተባባሪው እንዲወድቅ የተወሰነበትን የጥናት ወረቀት ውሳኔው ከመተላለፉ በፊት የምክንያቱን አሳማኝነት ያጣራል፡፡

## ፩.፬. የተካቶ መወሰኛ መመሪያ (Acceptance or Notability Guideline)

- በተሰጠው ርእስ ዙሪያ አስፈላጊ ነጥቦች የተካተቱበት መሆኑ (Significant Coverage)- (በውጭ አርትዖት መመሪያ ሥር ይዘት የሚለውን ንዑስ ርእስ ተመልከት)

- ተገቢ የሆኑ የመረጃ ምንጮች የተካተቱበት (Reliable sources) - ተገቢው ማለት በቤተ ክርስቲያኗ ወይንም በዓለማዊው

  መስፈርት የተሻለ ደረጃውን የጠበቀ ማለት ነው፡፡

- ግለሰባዊ ይዞታ የሌላቸው የጥናት ወረቆችን የተጠቀሙ (Independent of the Subject) ወይንም ግለሰቦች ወይንም ቡድኖችን በተለየ ሁኔታ የሚያንኳስሱ (የሚያጥላሉ) ወይም

የሚያሞግሱ የጥናት ወረቀቶችን በመረጃ ምንጭነት ያልተጠቀሙ ሲሆን

- በመሰለኝ ያልተጠናቀሩ መረጃዎች (Presumed) ያላካተተ መሆን አለበት፡፡
- እነዚህን እና ሌሎች በአርትዖት መመሪያው ላይ በዝርዝር የቀረቡትን ነጥቦች ያሟላ ጥናት ተቀባይ ይኖረዋል፡፡
- አስተያየት ተሰጥቶት በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተስተካከለ ጥናት ከሆነ በአጠቃላይ በመመሪያው መሰረት የተገመገመ ጽሑፍ ከአራቱ አንዱ ደረጃ ይሰጠዋል፤ እነሱም

ሀ. እንዳለ ተቀባይነት ያገኘ

ለ. ከጥቂት ማስተካከያ ጋር ተቀባይነት ያገኘ

ሐ. ከከፍተኛ ማስተካከያ ጋር ተቀባይነት ያገኘ

መ. ውድቅ የተደረገ

**፪. የቅበላ መመሪያ**(Submission or External Editorial Guideline)

የውጭ አርትዖት መመሪያው በዋናነት በሥሩ ሁለት መመሪያዎችን የሚያቅፍ ሲሆን እነሱም የይዘት መመሪያ(Content Guideline) እና የአጻጻፍ ስልት መመሪያ(Writing Style Guideline) ናቸው፡፡ ዝርዝር መመሪያው እንደሚተለው ይቀርባል

- **ይዘት**
  - በመዝገበ እእምሮው ውስጥ እንዲታተሙ የሚመረጡ የጥናት ውጤቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ እውቀት ማለትም ሐሳብ፣ ቀኖና ፣ትውፊት፣ ታሪክ፣ ሥርዓት፣ ዕውቀቶች፣ ሊቃውንትና አባቶች የሚዳስሱ መሆን አለባቸው፡፡
  - ቃሉ የተገኘበትንና ተሸክሞት የቆመውን ሀሳብ (Etymology meaning) የሚገልጽ መሆን አለበት
  - የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማወዳደር ተገቢውን ብያኔ(Definition) የሰጠ መሆን አለበት

- የተመረጠው ዐቢይ ቃል ወይንም ሐረግ ታሪካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ይዘት በተለይም ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር (Historical, Cultural, Economic, Social and Political Overviews) የተቃኘ መሆን አለበት፡፡
- የተመረጠው ርእሰ(ስረይ)ቃል በውስጡ የሚይዛቸው መሠረታዊ አላባውያንን (Elements) በአግባቡ የተተነተነና ማስረጃ የቀረበበት ሊሆን ይገባል ፡፡
- የተውጣጡት አላባውያንን በቡድን ለማወዳደር ወይንም ለማዋገን እንዲያመች በመከፋፈል (Classification) ራሱን የቻለ ፍሰት ባለው መልኩ የተደራጁ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡
- ከላይ የቀረቡት ጥቅል ሁኔታዎች አንድምታቸው የተፍታታበት ወይም የተተረጎመበት(Interpretation) ሊሆን ይገባል፡፡
- የጥናት ወረቀቶቹ ዓይነት ጠንካራ ከሆነ የተዛምጅ ሥራዎች ቅኝት (Empirical Literature Review) የተገኙና ከላይ በተዘረዘረው መሠረት ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

- **በመዝገበ አእምሮው ሊካተቱ የሚችሉ የጥናት ወረቀቶች ሊከተሉት የሚገባ ቅርጽና አጻጻፍ ስልት( Writing Style and Format)**

**፩. አወቃቀር**

- የተመረጠው የጥናት ወረቀት የርእስ ገጽ(Title Page) ሊኖራቸው ይገባል፣
- የጥናቱ ዋና አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣ ገላጭ የሆኑ ሥዕሎችንና ርእሶችን ሊይዝ ይችላል፡፡
- ጥናቱ የማጣቀሻ መጻሕፍት ዝርዝር (References) ሊዘጋጅለት ይገባል፣ የማጠቃሻ መጽሓፍት ዝርዝሩ Unified Style Sheet for Linguistics and Philology ስልት የተከተለ መሆን አለበት (ለተጨማሪ መረጃ አባሪውን መመልከት ይቻላል)፡፡
- ጥናቱ ካለቀ በኋላ በ Microsoft word format ላይ መቀመጥ አለበት
- የጥናቱን አንቀጾች ሲጻፍ ወደውስጥ ገባ (Indent) ብሎ መጀመር የለበትም፣ በሌላ አገላለጽ block style ይጠቀማል ማለት ነው፡፡

በሁለቱ ተከታታይ አንቀጾች መኻል ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ የአንድ መስመር ያህል ቦታ ይተዋል፡፡

- የሚዘጋጀውን የጥናት ወረቀት የገጽ ቁጥር አንሰጠውም፤ ምክንያቱም በዋናው ጥራዝ ሲካተት የተለየ ገጽ ሊኖራቸው ስለሚችል ነው፡፡

## ፪. የፊደል መጠን፣ ዓይነት፣ በመስመሮች መኻከል ሊኖር የሚገባ ክፍተትና ርእስ

- ሁሉም የጥናት ወረቀቶች በአማርኛ ይዘጋጃሉ
- በተከታታይ መስመሮች መኻከል 1.5 ያኽል ክፍተት ሊኖረው ይገባል፣
- የጥናት ወረቀቶቹ ሲዘጋጁ የአመርኛ ፊደልን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
  - ነገር ግን የግዕዝ ቃላትን በጥናቱ ውስጥ ሲካተቱ የኢቶፒክ እስክሪፕትን(Ethiopic Script or Geez Orthography) ተገቢውን አገባባቸው ማወቅና መጠቀም ይገባል፡፡ ምክንያቱም የትርጉም ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ በመሆናቸው ነው፡፡
    ምሳሌ- ሰረቀ---------ገንዘብ ወሰደ
    ሠረቀ-------- ወጣ፣ ታየ

ፊደላቱ የትርጉም ለውጥ ቢያመጡም ባያመጡም ፊደላቱን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ምሳሌ - ሥራ እና ስራ፡፡

- በጥናቱ ውስጥ የመጀመሪያ ርእስ ኀላ ከተደረገ በኋላ(Bold) በ11 የፊደል መጠን(Font size) ይጻፋል፡፡
- ሁለተኛው ርእስ ኀላ ከተደረገ በኋላ(Bold) ወደ ኢታሊክስ (italics)ተቀይሮ በ11መጠን(Font) ይጻፋል፡፡
- የተቀረው የጽሑፍ አካል በ11 መጠን(font size) ያለው ሆኖ በቪዥዋል ግዕዝ ዩኒኮድ (Visual Geez Unicode) ይጻፋል፡፡

## ፫. ማስታወሻ አወሳሰድን በተመለከተ

- በመዝገበ አእምሮው ውስጥ እንዲካተቱ የሚመረጡ የጥናት ወረቀቶች የግርጌም ይሁን የራስጌ ማስታወሻ አይኖራቸውም፡፡
- በጥናቱ ውስጥ ከሌሎች የታወቁ ምንጮች ሐረጋትን ዓረፍተ ነገሮችን ወይንም አንቀጾችን ስንወስድ፡-
  1. ጭምቅ መንገድን መከተል ተመራጭ ሲሆን ነገር ግን
     1.1. የተባለውን ወይንም የተጻፈውን እንዳለ በመውሰድ የጥናቱ አካል አድርጎ ለማካተት ከተፈለገ ፤ እስከ 3 መስመር የሚሆነውን በጥናቱ ውስጥ የትእምርተ ጥቅስ (“ ”) ምልክት በመጠቀም ማካተት
     1.2. ከሦስት መስመር በላይ የሚሆን ከሆነ ከዋናው አካል በተወሰነ ከቀኝም ከግራም የአንድ ቃል ያህል ቦታ ገባ በማለት ይቀመጣል፡፡ ጽሑፉ *Italicised* ይሆናል፡፡
- በጥናቱ ውስጥ ማስታወሻዎችን ከወሰድን በኋላ የጸሓፊው ሙሉ ስም ማለት-
  - በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ስም እና የአባት ስም( First Name and Father’s Name)
  - የውጭዎች ከሆነ ደግሞ የመጀመሪያ ስም እና የቤተሰብ ስም( First name and Family name) ይጻፋል፡፡
- ሙሉ ስም ከተጻፈ በኋላ ዐመተ ምሕረት በቅንፍ ( ) ምልክት ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡
- የተወሰደው ሐረግ ወይንም ዓረፍተ ነገር ከመጻፉ በፊት የወሰደበትን ምንጭ ለመጥቀስ የምንፈልግ ከሆነ የጸሓፊውን ስም ከ ቅንፍ ውጭ በማድረግ ዓ.ም በቅንፍ ውስጥ በማድረግ ይጻፋል፡፡

ምሳሌ

ቸርነት አበበ (1999) የሰባው ሊቃናት ትርጉም የምንለው ከጥንት ከዕብራይስጥ ቋንቋ የተተረጎመውን ያልተበረዘውን የመጀመሪያ ትርጉም ማለታችን ነው ፡፡

- ነገር ግን የምንፈልገውን ዓረፍተ ነገር ወይንም ሐረግ ከወሰድን በኋላ የጸሓፊውን ስም የምንጽፍ ከሆነ ሙሉ ስሙንም ዓ.ም በቅንፍ ውስጥ እናስቀምጣቸዋል፡፡ በስሙ እና በ ዓ.ም መካከል ነጠላ ሰረዝ እንጠቀማለን፡፡

ምሳሌ

የሰብዓው ሊቃናት ትርጉም የምንለው ከጥንት ከዕብራይስጥ ቋንቋ የተተረጎመውን ያልተበረዘውን የመጀመሪያ ትርጉም ማለታችን ነው (ቸርነት አበበ፣ 1999) ፡፡

- መረጃውን በጭምቅ(Summery) መንገድም ይሁን በቀጥተኛ (direct quote) መንገድ ከወሰድን በኋላ የጸሓፊውን ሙሉ ስም ወይንም የተገኘበትን ቦታ እና ዓ.ም ከማስቀመጥ ውጭ መረጃው የተገኘበትን ገጽ አናካትትም፡፡

### ፬. የገጽ ብዛትን በተመለከተ

- በመዝገበ አእምሮው ውስጥ እንዲካተቱ የተመረጡ ጽሑፎች የገጽ ብዛት ከፍተኛው 10 ገጽ ሲሆን ዝቅተኛው 11/2 ገጽ ነው፡፡
- ነገር ግን ከ 10 ገጽ የሚበልጥ ከሆነ ጸሐፊው/ዋ የጻፉበትን ነፍሰጡር ቃላት(lexical entries) ሌላ ንዑሳን ቃላትን ሐረጋት( sub entry) በማዋጣት ሊከፍሉት ይገባል፡፡

ምሳሌ - **ላሊበላ** በሚለው ቃል መጻፍ ብንፈልግ 30 እና 40 ገጾችን ሊጻፍ ይችላል፡፡ ስለዚህ **ላሊበላ** በሚለው ሥር ወጥ በሆነ መንገድ ብዙ ገጾችን ከመጻፍ ይልቅ ሌሎች ንዑሳን ርእሶችን በመፍጠር ይከፋፈላል ፡፡

- ላሊበላ ንጉሡ
- ላሊበላ የቦታው ስያሜ
- ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናቱ
- ላሊበላ በመባል የሚታወቀው ማኅበረሰብ ወዘተ. በማለት በንኡሳን ርእሶች መከፋፈል ይቻላል ማለት ነው፡፡

- ከ 11/2 ገጽ በታች ሲሆን ይቀርበዋል ተብሎ ወደሚታሰበው ዐቢይ ቃል ሥር በመውሰድ ንዑስ ርእስ እንዲሆን ይደረጋል፡፡አንዳንድ

ነፍሰጡር ቃላት ብቻቸውን በቆመው ብዙ ሊያጽፉ የማይችሉ በመሆናቸው ምክንያት ሁልጊዜም ላይሆን ይችላል፡፡

## ፩. አሕጽሮቶች (abbreviation) እና ምልክቶች አጠቃቀም

### 1. አሕጽሮቶች አጠቃቀም

- በጥናቱ ውስጥ የምንጠቀማቸው አሕጽሮቶች መሆን አለባቸው፣

ምሳሌ- **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን -** ኢ.ኦ.ተ.ቤ. ማለት መቻል አለበት

- ነገር ግን በጥናቱ ውስጥ ዐቢይ ቃል በመሆን የሚያገለግለውን ወይም ንዑስ ዐቢይ ቃል በመሆን የሚያገለግለውን ቃል፣ ሐረግ ወይም ጥምር ስም ከሆነ ደጋግሞ ከሚጻፍ ይልቅ አሳጥሮ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡ይህ ማለት መጀመሪያ ሙሉውን ጽፎ በቅንፍ ምልክት( ) አህጽሮቱ ከተጻፈ በኋላ በቀጣይ ቃሉ ሲገኝ አህጽሮቱን ብቻ መጠቀም ይቻላል፡፡

ምሳሌ- **ሀገረ ማርያም** ሀ.ማ. ይወክለዋል ማለት ነው

በአማርኛ ሀለሐመ የፊደል ገበታ ሥርዓት በመጠቀም የተመረጠው ቃል በተገለጸው ሥርዓት ተራው ደርሶት በርእሱ ዙሪያ ከተጻፈ በኋላና ተጨማሪ ጉዳዮችን ማንሣት ቢፈለግ ጉዳዮቹ በሚነሡበት ቦታ በግልጽ የተብራሩ መሆኑናቸውን ለመግለጽ ሰሜን ምስራቃዊ ምልክት (North East Arrow or Up right Arrow) (↗) እንጠቀማለን፡፡

ምሳሌ፤ **ሀገር** በሚለው ነፍሰጡር ቃል ተገቢውን ጽሑፍ ከተዘጋጀ በኋላ ሀገረ **ናግራን** የሚል ሀረግ በምሳሌነት ብንጠቀምበት በዝርዝር ሌላ ቦታ መገለጹን በሁለት መንገድ ማስረዳት እንችላለን ፡-

- በጽሑፋችን መኻል ላይ ቃሉን ከተጠቀምንበት

  ***ሀገረ ↗ናግራን*** በማለት ስንገልጸው
- ጽሑፋችንን ካጠናቀቅን በኋላ ከሆነ ደግሞ በሚከተለው መልኩ እናስቀምጠዋለን

***ሀገረ ናግራን*** *↗ናግራን*